ሕግ ለደህንነት ጠቃሚ ነው - ደህንነትዎ የተጠበቀ እንዲሆን ነው ፍላጎታችን

## ወደ ስኮትላንድ እንኳን በደህና መጡ

# ስለ ስኮትላንድ ሕግ መመሪያ

ኒው ኮሌጅ ላነርሻየር የ ኤች ኤን ዲ የሕግ ኣገልግሎት ተማሪዎች;
የፍርድ ቤት ጽሕፈት ቤት;ፕሮኪዩሬተር ፊስካል (ሕጋዊ የመንግስት ድርጅት) እና
የስኮትላንድ ፖሊስ በጋራ ያዘጋጁት ፕሮጀክት

New College Lanarkshire

CROWN OFFICE
& PROCURATOR
FISCAL SERVICE
SCOTLAND'S PROSECUTION SERVICE

POLICE
SCOTLAND
Keeping people safe

## ምስጋና

ይህ መጽሃፍ ሊታተም የበቃው በሚከተሉት እርዳታ እና አስተዋጽኦ ነው፡

ኒው ኮሌጅ ላነርሻየር

የፍርድ ቤት ጽሕፈት ቤት እና ፕሮኪዩሬተር ፊስካል

የስኮትላንድ ፖሊስ

ስኮቲሽ ሬፈዩጂ ካውንስል

ሜሪሂል የመዋሃድ አውታር

ዘብሪጅስ ፕሮግራም

**ለሚከተሉት የተለየ ምስጋና እናቀርባለን**

ክቡር ፍራንክ ሙልሆላንድ ኪውሲ; ሎርድ ኣድቮኬት (የወንጀል ምርመራ ክፍል ዋና ሚንስተር )

የኤች ኤን ዲ የሕግ ኣገልግሎት ተማሪዎች

ኤለኖር ላፍረቲ (የሕግ ኣስተማሪ; ኒው ኮሌጅ ላነርሻየር)

ሜሪ ኒኮልሰን (የስርኣተ ትምህርት እና ጥራት ሃላፊ; ኒው ኮሌጅ ላነርሻየር)

ካረን ዩዊል (የፕሮጀክት ሃላፊ እና የቡድን ሃላፊ)

ሎረን ሚለር (የቡድን ሃላፊ)

ኒኮል ዎከር (የቡድን ሃላፊ)

ሴራ ቲሩዌዝ (የስነ ጥበብ ስእል እና የቡድን ሃላፊ)

ጀማ ዋሌስ (ስነ ጥበብ እና ስእል)

ጆሽ  ከርክላንድ (የህትመት  ክፍል)

ኣምበር ራፈርቲ (የመጽሃፍ ሽፋን ዲዛይን)

ጋሪ ስታርክ (ግራፊክ ዲዛይነር; ኒው ኮሌጅ ላነርሻየር)

ጆን ካይል (የሕግ ሰራተኛ)

ፒተር መክላንድ (የሕግ ሰራተኛ)

ገርቲ ዋሌስ (የሕግ ሰራተኛ)

ዳርዮ ዳንድሪያ (የስኮትላንድ ፖሊስ )

ስኮትላንድ ውስጥ ያሉ ስደተኛ ማህበረሰቦችም ይህንን ማስረጃ የሚሰጥ ወረቀት እንድናዘጋጅ ስለተባበሩን እና ስለረዱን ልናመሰግናቸው እንወዳለን።

**ወደ አገራችን እንኳን በደና መጣችሁ እያልን ስኮትላንድ ውስጥ ለሚጀምሩት አዲስ ህይወትዎ ሁሉም መልካም እንዲያጋጥሞት እንመኝሎታለን።**



## መግቢያ



የኒው ኮሌጅ ላነርሻየር (ማዘርዌል ካምፓስ) ኤች ኤን ዲ  የሕግ ኣገልግሎት ተማሪዎች ወደ ስኮትላንድ ለመኖር ለሚመጡት ስደተኞች መመርያ እንዲሆናቸው ብለው ይህንን ማስረጃ የሚሰጥ ወረቀት በማዘጋጀታቸው ድጋፌን እገልጻለው።

ይህ ፕሮጀክት በሙሉ ልቤ የተማመንኩበት ነው; ሃሳቡም የመነጨው እንደ ኣጋጣሚ ሆኖ ፍርድ ቤት እኔ በክስ አቅርቤው የነበርኩትን ጉዳይ ለማየት ከመጡ ተማሪዎች እና ሰራተኞች ጋር በተገናኘንበት ወቅት ነው። በፍርዱ የእረፍት ግዜ ከተማሪዎቹ ጋር እየተነጋገርን ሳለ ነው ይህንን ማስረጃ የሚሰጥ ወረቀት ለማዘጋጀት ሃሳብ የመነጨው። ከዛን ግዜ ጀምሮ ተማሪዎቹ ይህንን ማስረጃ የሚሰጥ ወረቀት ለማዘጋጀት የሚያረጉት ጥረት እና ታታሪነት በጣም የሚገርም እና የሚያበረታታ ነበር። ይህ ማስረጃ የሚሰጥ ወረቀት ለመረዳት ከባድ በሆነ ሁኔታ በማህበራዊ አገልግሎት ሰጪዎች ከሚዘጋጅ ይልቅ; ወደ ኣገራችን ለመጀመሪያ ግዜ ለሚመጡ ሰዎች ስለ ስኮትላንድ ኣንዳንድ ዋና ጠቃሚ እና ተግባራዊ ነገሮችን እንዲያውቁ በማለት ቀላል በሆነ እና ሁሉም ሰው ሊገባው በሚችል መንገድ ስለ ስኮትላንድ ሕግ የሚያስረዳ በስኮትላንዳውያን ዜጎች የተዘጋጀ ማስረጃ የሚሰጥ ወረቀት ነው።

ወደ አንድ ኣገር ለመጀመሪያ ግዜ መጥቶ ሕይወትን እንደ አዲስ መጀመር ከባድ እና የሚያሳስብ ሊሆን ይችላል የአገሩ መመሪያዎች እና ሕጎችም ሁልግዜ በቀላሉ ላይገኙ ይችላሉ። ይህ መመሪያ ደግሞ ስኮትላንድ ውስጥ ማዳላትን ለማጥፋት ስኮትላንድ ውስጥ ብዙ ኣመታት ለኖረ ሰውም ሆነ የተወሰነ ቀናት ለኖረ ሰው ሁሉንም ሰው በኣንድ ላይ ለማጠቃለል የሚደረገውን የበጎ ኣድራጎት ስራ የሚያሳይ ኣንዱ ምሳሌ ነው። ተማሪዎቹ እና ሰራተኞቹ ይህንን መመሪያ ለማዘጋጀት ላደረጉት ጥረት ሁሉ ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

**የተከበሩ ፍራንክ ሙልሆላንድ ኪውሲ;**
ሎርድ አድቮኬት



# ማውጫዎች

**ቤተሰብ ........................................6**
ትዳር ........................................6
ፍቺ ........................................6
የወላጅ ሃላፊነቶች ........................................6
የቤት ውስጥ በደል ........................................7
እርግዝና እና እርግዝናን ማስወረድ ....8
ኣዋረድከን በማለት የሚደረግ ጥቃት ........................................8
የሴት ልጅ ግርዛት ........................................8

**የአገሩ ሕግ ........................................10**
መጠጥ ........................................10
ሲጋራ ........................................10
የቴሌቪዥን ፍቃድ ........................................10
የገንዘብ ብድር ........................................10

**የመንገድ ላይ ሕግ ........................ 12**
ለማህበረሰብ-ተጻራሪ ባህሪ ...............12
ሰውን ማስፈራራት እና አመጽ ማነሳሳት ........................................12
ቆሻሻ በመንገድ ላይ መጣል ..............13
ህዝብ በሚበዛበት ቦታ ዕርቃነ ስጋን ማሳየት ........................................13
አስቁሞ መፈተሽ ........................................13
የእግረኛን መንገድ መጠቀም.............13

**የመኪናዎች እና የሞተር ብስክሌት ሕጎች ........................ 15**

**የስራ ቦታ ሕጎች ........................ 18**


**የወንጀል ሰለባ ለሆኑ - ስኮትላንድ ውስጥ ወንጀል የሚባሉ .............20**
ጥቃት ........................................21
ጠመንጃ እና ሽጉጥ ........................................21
የሚጎዱ መሳርያዎች ........................................21
ግብረስጋ ነክ ወንጀል ........................22
ሽርሙጥና ........................................22
በጥላቻ የሚደረግ ወንጀል ...............23
ለጥቅም ብሎ ሰውን በኮንትሮባንድ ማሸጋገር ........................................24
ኣደንዛዥ እጽ እንደ ሃሺሽ ...............24
በሕገወጥ መንገድ ገንዘብ ማሸጋገር .24
ስርቆት ........................................25
የኢንተርኔት መገናኛ እንደ ፌስቡክ ........................................25
በእንስሶች ላይ በደል ማድረስ.........25

**የወንጀል ሰለባ ለሆኑ የሚሰጥ እርዳታ ........................28**

**ሕጋዊ ማስረጃ ........................28**



# ቤተሰብ



# ቤተሰብ

## ትዳር

ኣንድ ሰው ዕድሜው 16 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ሊያገባ ይችላል። ይህ ማለት ደግሞ ተቃራኒ ጻታ ያላቸው ጥንዶች ሆኑ ኣንድ ኣይነት ጾታ ያላቸው ጥንዶች ሊጋቡ ይችላሉ።

በአንድ ግዜ ከአንድ ሰው በላይ ማግባት ሕግ ኣይፈቅደውም።

## ፍቺ

በትዳር ለመኖር ፍላጎት ከሌለዎት በተወሰኑ ሁኔታዎች ምክንያት ሊፋቱ ይችላሉ። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ዝሙት; ያልተለመደ ባህሪያት ወይም ደግሞ ለረጅም ግዜ ተለያይተው ሲኖሩ ከቆዩ።

## የወላጅ ሓላፊነቶች

ስለ ልጆችዎ ደህንነት ሓላፊነት ሊኖርዎት እና የልጆችዎን ደህንነት ሊጠብቁ ይገባል። አንድ ወላጅ ልጆቹን ያለጠባቂ በማንኛውም ግዜ እቤት ውስጥም ሆነ ሌላ ቦታ ብቻቸውን መተው የለበትም። አንድ ልጅ ከ 16 በታች ከሆነ ለሊት ብቻውን እቤት ውስጥ በፍጹም መተው የለበትም።

የወለዱዋቸውን ልጆችዎ ወይም ደግሞ የሚያሳድጓቸውን ልጆች ከመቱዋቸው ሊከሰሱ ይችላሉ። በተለይ ደግሞ ልጅን እራሱ ላይ ከመቱት; በሃይል ከነቀነቁት ወይ ደግሞ በሆነ እቃ ከመቱት; ሕግ ተላልፈዋል ማለት ነው። ልጅን መምታት ኣካላዊ እና አእምሮኣዊ ጉዳት ሊያስከትል ይይችላል; ለወደፊትም ሕይወታቸው ላይ ችግር ሊያስከትል ይችላል።

ልጆችዎ ዕድሚያቸው 5 ሲሞላ ትምህርት ቤት ሊያስገቡዋቸው ይገባል፡ ይህ ሕጉ ስለሆነ ካላስገቡዋቸው እንደ ወንጀል ነው የሚቆጠረው። ኣንድ ልጅ ወደ ትምህርት ቤት ሁልጊዜ ሊሄድ ይገባል; ኣለበለዚያ ግን ወላጆች በሕግ ሊቀጡ ይችላሉ። ይህም ደግሞ ልጁ ስንት ግዜ እንደ ቀረ በማየት እና እቤት ውስጥ ያለውን ሁኔታዎች ታይቶ ውሳኔ ይሰጣል።



## የቤት ውስጥ በደል

የቤት ውስጥ በደል ማለት ኣንድ ሰው ጓደኝነት ወይም ዝምድና ካለው ሰው ጋር (ወይ ደግሞ ከነበረው) ሰው መጠቃት ወይ በደል ሲደርስበት ማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ የግድ ለተለያዩ ጾታ ያላቸው ጥምድ በኣንድ ላይ በአንድ ቤት ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ብቻ ይሚመለከት ኣይደለም። ሴት ልጆችም ሆኑ ወንዶች የቤት ውስጥ በደል ሊያጋጥማቸው ይችላል። ይህ ማለት ደግሞ ሴቶች ወንዶች ላይ የቤት ውስጥ በደል ሲያደርሱ እና በኣንድ ኣይነት ጾታ ያላቸውም ጥንድ ወይ ከዝህ በፊት ግንኙነት በነበራቸው መካከልም ማለት ነው።

የቤት ውስጥ በደል ተብለው የሚታዩ ወንጀሎች የተለያዩ ብዙ ኣይነቶች ሊሆኑ ይችላሉ; እንደ ኣንድ ሰው ላይ ኣካላዊ ጉዳት; ግብረስጋዊ ጥቃት; ስሜታዊ እና ስነኣእምሮኣዊ ጉዳት ማድረስ። ፖሊስ የቤት ውስጥ በደል ወንጀልን በከፍተኛ ሁኔታ ነው ይሚከታተሉት። ለፖሊስ የተጠቆመን ወንጀል በተቻለ መጠን በኣስቸኳይ ፖሊስ እንዲከታተሉት ይደረጋል። የቤት ውስጥ በደል ወንጀል ጥቆማ በተደረገበት ወቅት ፖሊስ የመጀመርያ ዋና ሃላፊነታቸው የወንጀሉ ሰለባ የሆኑትን ደህንነት ማረጋገጥ; የቤተሰቦቻቸውን እና ሌላ ከእነሱ ጋር የነበረውንም ሰው ደህንነት ማረጋገጥ ነው።

ስለ ወንጀሉ በቂ መረጋገጫ ከተገኘ ወንጀለኛው ይከሰሳል ፍርድ ቤትም እስኪቀርብ ድረስ ሊታሰር ይችላል።



## እርግዝና እና እርግዝናን ማስወረድ

ስለ እርግዝና በተመለከተ ማስረጃ የሚከተለው ድረገጽ ላይ ሊገኝ ይችላል **www.readysteadybaby.org.uk** ወይ ደግሞ ወደ ኤንኤችኤስ(የጤና ኣገልግሎት) በስልክ ቁጥር 111 ሊደውሉ ይ ችላሉ።

እርግዝናውን የማይፈልጉ ከሆነ እና እርግዝናውን ለማስወረድ የሚያስቡ ከሆነ ይግድ በኣስቸኳይ  የጤና ምክር ኣገልግሎት ማግኘት ኣለቦት።

## ኣዋረድን በማለት ይሚደረግ ጥቃት

አዋረድከን ተብሎ የሚደረግ ጥቃት የኣንድ ቤተሰብን ወይ ደግሞ የማህበረሰብን ክብር እንዳይነካ ወይ ደግሞ ለማስከበር በማለት በሌሎች ሰዎች ላይ የሚደረግ ወይ ደግሞ የተደረገ ጥቃት ነው። ሁልጊዜ ሳይሆን ኣብዛኛውን ግዜ ግን በሴቶች ላይ ወይም ደግሞ በልጅኣገረዶች ላይ በቤተሰቦቻቸው ወይም ደግሞ በማህበረሰቡ የሚደረግ ጥቃት ነው።

'ኣዋረድከን ተብሎ የሚደረግ ወንጀል' ኣብዛኛውን ግዜ የሚፈጸመው ሰለባ የሆነው ሰው ወይም ሰዎች ያደረጉት ተግባር በቤተሰቡ ላይ ወይ ደግሞ በማህበረሰቡ ላይ ውርደት ሊያመጣ ይችላል በሚል ኣስተሳሰብ ነው። ፖሊስ ኣዋረድከን ተብሎ የሚደረግን ጥቃት በከፍተኛ ሃላፊነት ነው የሚያየው ምርመራውንም ጥብቅ በሆነ መንገድ ነው የሚያካሂዱት።

ኣንድን ሰው ኣስገድዶ መዳር እንደ ኣንድ ኣዋረድከን ተብሎ የሚደረግ ጥቃት ነው የሚቆጠረው ስኮትላንድ ውስጥም ኣንድን ሰው ኣስገድዶ  መዳር እንደ ኣንድ ኣዋረድከን ተብሎ የሚደረግ ወንጀል ነው የሚታየው።

## የሴት ልጅ ግርዛት  (ኤፍጂኤም)

የሴት ልጅ ግርዛት (ኣንዳንዴም የሴትን ልጅ ብልት መቁረጥ ተብሎ የሚታወቀው) የሴት ልጅ ብልት ላይ በህክምና ባልሆነ መንገድ ለውጥ ሊያስከትል እና ጉዳትም ሊያመጣ የሚችል ኣሰራር ነው። ይህ ኣሰራር በጣም ህመም የበዛበት እና በሚቆረጥበት ግዜ ሆነ ለወደፊት በሕይወት ላይ ከባድ የጠና ችግር ሊያመጣ የሚችል ነው። ይህ ኣሰራር በእንግሊዝ ኣገር ውስጥ ሕገወጥ ነው። ሴትን ልጅ ውጪ ኣገር ኣስገርዞ መምጣትም ሕገወጥ ነው።



# የአገሩ ሕግ



# የአገሩ ሕግ

## መጠጥ

ስኮትላንድን እና እንግሊዝ ኣገር ውስጥ መጠጥ ለመሸጥ ፍቃድ የተሰጣቸው ቦታዎች ብቻ ናቸው መሸጥ የሚችሉት ለመግዛት የሚፈቀድለትም እድሜው 18 የሞላ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ሰው ብቻ ነው።

ከ 18 ኣመት በታች ለሆነ ሰው መጠጥ ገዝቶ መስጠት ወይም ለመግዛት መሞከር ወንጀል ነው። ከ 18 ኣመት በታች ለሆነ ሰው መጠጥ መሸጥ ወንጀል ነው።

መጠጥ ለመግዛት እንደሚፈቀድሎት እና 18 ኣመት እንደሞላዎት ኣንዳንድ ማስረጃዎች እንደ የመታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ወይም ደግሞ የመንጃ ፈቃድ ሊያሳዩ ይገባል።

## ሲጋራ

ሲጋራ ወይም ሌላ እንደ ትምባሆ ኣይነት ለመግዛት የሚፈቀድለት እድሜው 18 የሞላው ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ሰው ብቻ ነው። ትምባሆ ማለት የሚያጠቃልለው ደግሞ እንደ ሲጋራ; ሲጋር; ብትን ሆኖ የሚሸጥ በእጅ የሚጠቀለል ትምባሆ ኤሌክትሮኒካዊ ሲጋራን እና የሚታኘክ ሲጋራን ነው።

ብዙ ግዜ ህዝብ የሚሰበሰብበት ቦታ እና የስራ ቦታ ላይ ሲጋራ ማጨስ ሕገወጥ ነው እንዲሁም እድሜያቸው ከ 18 ኣመት በታች ለሆኑ እንደ ትምባሆ ኣይነት ገዝቶ መስጠት ሕገወጥ ነው።

የሆነ እንደ ትምባሆ ኣይነት ልትገዙ የሚገባዎት ከሱቅ ውስጥ ብቻ ነው።

## የቴሌቪዥን ፍቃድ

እቤት ውስጥ ቴሌቪዥን ካሎት እና በቀጥታ የሚተላለፍ ቴሌቪዥን ፕሮግራም የሚያዩ ወይም የሚቀዱ ከሆነ የቴሌቪዥን ፍቃድ ከፍለው ማውጣት ኣለቦት። ቴሌቪዥኑን ግን የቴሌቪዥን ፕሮግራም የማያዩበት ከሆነ እና የሚጠቀሙበት ዲቪዲ ለማየት እና ቪዲዮ ጌም ለመጫወት ብቻ ከሆነ የቴሌቪዥን ፍቃድ ሳይከፍሉ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

## የገንዘብ ብድር

የገንዘብ ብድር ከፈለጉ ሕጋዊ ከሆነ ድርጅት ብቻ ነው መበደር ያለቦት።



# የመንገድ ላይ ሕግ




# የመንገድ ላይ ሕግ

## ለማህበረሰብ-ተጻራሪ ባህሪ

ረበሻን የሚያነሳሳ ባህሪ ማለት ሌሎችን ማስፈራራት እና ሌሎችን የሚያስጨንቅ ሁኔታዎችን መፈጸም ነው።

ጻረ ማህበረሰብ ባህሪ የሚያጠቃልለው፡

- የድምጽ ረብሻ
- ቅጥ የሌው ባህሪ እንደ ጩህት; ባለጌ ንግግር እና ጥል
- ጎረቤትን ሆነ ሌሎችን ማስፈራራት
- ስድብ
- ሌሎችን ሊያስጨንቅ እና ሊያስፈራራ የሚችል ተግባር እና ጥቃት መፈጸም ለምሳሌ ኣረጋውያን ላይ ወይም ደግሞ ኣካለ ስንኩላን ላይ
- የቤትን ቆሻሻ መንገድ ላይ ሆነ የጋራ ግቢ ውስጥ እና የኣትክልት ቦታ ላይ መጣል
- የሰውን ንብረት ማበላሸት



## ሰውን ማስፈራራት እና ኣመጽ ማነሳሳት

እነዚህ የሚከተሉትን ተግባሮች ሰው የሚሰበሰብበት ቦታዎች ላይ ማድረግ ኣይፈቀድም፡

- መንገድ ላይ ወይም ደግሞ ሌላ የሆነ ሰው የተሰበሰበበት ቦታ መጠጥ መጠጣት፡ መንገድ ላይ ብዙ ቦታዎች መጠጥ መጠጣት ሕገወጥ ነው።
- ኣንድ ላይ ብዙ ሆኖ ወይም በቡድን መሰብሰብ፡ እንደዚህ ኣይነት መሰብሰብ የሚያስፈራ ሆኖ ሊታይ ስለሚችል ከተቻለ ብዙ ሆነው ኣይሰብሰቡ
- ሰው የተሰበሰበበት ቦታ ጩህት; ረብሻ እና ባለጌ ኣነጋገር
- ሌሎችን ሊያስጨንቅ እና ሊያስፈራራ የሚችል ተግባር እና ጥቃት መፈጸም

እንደዚህ ኣይነት ባህሪ መፈጸም በፖሊስ ሊያሳስር ይችላል እንደ ወንጀል ታይቶም ሊያስከስስ ይችላል። ከታሰሩ ከፖሊስ ጋር ሊተባበሩ ይገባል።

## ቆሻሻ መንገድ ላይ መጣል

ቆሻሻ መንገድ ላይ ከጣሉ መቀጫ እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ ካልከፈሉ ደግሞ ተጨማሪ መቀጫ  እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ። ብዛት ያለው ቆሻሻ ደግሞ ከሆነ የባሰ ኣሳሳቢ ሁኔታ ስለሆነ በዚህ ወንጀል ከተያዙ ብዙ የገንዘብ መቀጫ  እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ።

## ህዝብ በሚበዛበት ቦታ ዕርቃነ ስጋን ማሳየት

እቤትዎ ውስጥ ብቻዎን ሲሆኑ የሚያደርጉት ነገር ሕጋዊ ይሁን እንጂ ሰው በተሰበሰበበት ቦታዎች ላይ ግን ሲያደርጉ ከተገኙ እናም በሌሎች ሰዎች ጎዳና ላይ ከታዩ እንደ ወንጀል ሊታይ ይችላል። የሆነ የግብረስጋ ነክ ግኑኝነት ኣይነት ባህሪ ሰው በተሰበሰበበት ቦታዎች ላይ ሲፈጽሙ ከተገኘ ወይም ደግሞ የሆነ ዕርቃነ ስጋ ወይም ብልትን ሰው በተሰበሰበበት ቦታዎች ላይ ማሳየት ወንጀል ነው።

## አስቁሞ መፈተሽ

ፖሊስ የሆነ እንዲይዙ የማይፈቀድሎትን እቃ እንደ ኣደንዛዥ ዕጽ (ሃሺሽ); ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መሳርያ ወይም ደግሞ የተሰረቀ እቃ ይዘው ይሆናል ብለው ከጠረጠሩ ኣስቁመው ሊፈትሹዎት ይችላሉ።

## የእግረኛን መንገድ ተጠቀም

ለጥንቃቄ ሲባል የእግረኛን መንገድ መጠቀምኣለቦት። የትራፊክ መብራት ያለበትን ቦታዎች ኣይተው መንገድ መሻገር ኣለቦት። ስኮትላንድ ውስጥ የሆነ የመንገድ ዳር ላይ ሊሄዱ ይፈቀድሎታል በሞተርዌይ (የመኪናዎች የፍጥነት ጎዳና ) ላይ ግን ኣይፈቀድም።

# የመኪናዎች እና የሞተር ብስክሌት ሕጎች




# የመኪናዎች እና የሞተር ብስክሌት ሕጎች

**የመኪና ጎዳና ላይ የሚመለከት ወንጀል የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡**

- ኣደጋ ሲያጋጥም ያለመቆም
- ብፍጥነት መንዳት
- መጠጥ ጠጥቶ ወይም እንደ ሃሺሽ የመሰሉትን ወስዶ መንዳት
- ያለ ጥንቃቄ በመንዳት ምክንያት ሰው ከገደሉ
- በኣደገኛ መንገድ መንዳት
- ሞባይል እየተጠቀሙ መንዳት
- ያለ ጥንቃቄ መንዳት
- ያለ ኢንሹራንስ (መድሕን) መኪና መንዳት
- ያለ መንጃ ፈቃድ ወይም  መንጃ ፈቃድ ተነጥቀው ሳለ መንዳት
- መብራት ቀይ እያለ መንዳት
- የመኪና ወምበር ቀበቶ ሳያስሩ መንዳት
- ኤምኦቲ (የመኪና ኣመታዊ ምርመራ) ሳያደርጉ መንዳት
- መኪና ችግር እያለባት መንዳት

እነዚህ እላይ ከተጠቀሱት ወንጀል የሆነውን ከፈጸሙ መቀጮ እንዲከፍሉ ሊመጣቦት ይችላል; የመቀጮ ነጥብ ሊመጣቦት ይችላል; እንዳይነዱ ሊታገዱ ይችላሉ ወይም ደግሞ የወንጀሉ ክብደት ታይቶ ሊታሰሩም ይችላሉ።


የመቀጮው ነጥብ ክብደት እና ወንጀሉ ታይቶ ለኣመታት የመንጃ ፍቃድዎ ላይ ሊቆይ ይችላል። ባለፉት 3 ኣመታት ውስጥ ከ 12 በላይ የመቀጮ ነጥብ ከተሰጠዎት ለ 6 ወር እንዳይነዱ ሊታገዱ ይችላሉ። በኣለፉት 2 ኣመት ውስጥ ከሆነ ፈተናዎን ያለፉት 6 ነጥብ ከተሰጥዎት እንዳይነዱ ሊታገዱ ይችላሉ።

ስኮትላንድ ውስጥ መኪና እና የሞተር ብስክሌት ለመንዳት የሚከተሉት ያስፈልጎታል:

- **ያልወደቀ የመንጃ ፍቃድ፡** ስኮትላንድ ወይም ደግሞ የሆነ እንግሊዝ ኣገር ውስጥ በሕጋዊ መንገ ለመንዳት 17 ኣመት ወይም ከዚያ በላይ መሆን ኣለቦት እንዲሁም ደግሞ የቃል ፈተና ማለፍ ኣለቦት። ወደ ስኮትላንድ ሲመጡ የውጪ ኣገር የመንጃ ፍቃድ ከነበሮት እናም ደግሞ የተሰጦት ኣገር ውስጥ ይሰራ ከነበረ የመንጃ ፍቃዱን ለ 12 ወራት ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ከ 12 ወራት በኋላ ደግሞ ለመንዳት ሙሉ የእንግሊዝ ኣገር የመንጃ ፍቃድ ፈተና ማድረግ ሊኖርቦት ይችላል።
- **የመንገድ ግብር፡** የመኪናዎን ግብር ሳይከፍሉ መንዳት ሕገወጥ ነው።
- **ኢንሹራንስ (መድሕን)፡** የመኪና መድሕን ሳይከፍሉ መንዳት ሕገወጥ ነው። እርስዎ ወይም ደግሞ ሌላ የሆነ ሰው መኪናዎን የሚጠቀም ካለ የመኪና መድሕን ውሉ ላይ ሁላችሁም መጠቀም እንደምትችሉ እንደጠቀሰ ኣረጋግጡ።
- **ኤምኦቲ (የመኪና ኣመታዊ ምርመራ)፡** ኤምኦቲ ማለት መኪናዎን በመንገድ ላይ ለመነዳት በቂ እንደሆነች የሚያረጋግጥ ሕጋዊ ወረቀት ነው። መኪና ያለ ኤምኦቲ መንዳት ሕገወጥ ነው።

ስኮትላንድ ላይ እየነዱ መጠጥ ለመጠጣት የሚፈቀደው መጠን በ 100 ሚሊሊትር ትንፋሽ ላይ ሊገኝ የሚፈቀደው የመጠጥ መጠን 22 ማይክሮ ግራም ነው። ኣንድ መጠጥ እንኳን ያልሞላ ከጠጡ የሚፈቀደውን መጠን ሊያልፉ ይችላሉ። ብዙ ጠጥጥ ጠጥተው ከነበረ በንጋታውም የሚፈቀደውን መጠን ሊያልፉ ይችላሉ። ስኮትላንድ ውስጥ ኣብዛኞቹ ሰዎች መኪና የሚነዱ ከሆነ መጠጥ ፈጽመው ኣይጠጡም በንጋታውም የሚነዱ ከሆነ መጠጥ በመጠኑ ብቻ ነው የሚጠጡት።

የመኪናዎ ጎማ ሁሉም የሚሰራ መሆን ኣለበት። የመኪና ጎማ ላይ ያለው ክርክር ጥልቀቱ በሕግ ሊሆን ከሚገባው 1.6 ሚሊሜ በታች መሆን የለበትም።





# የስራ ቦታ ሕጎች



# የስራ ቦታ ሕጎች

ስራ መቀጠር ማለት በኣጠቃላይ ኣሰሪው ለተቀጣሪው ለሚሰጠው ስራ እንዲከፍለው የሚያደርገው ስምምነት ነው። ይህ ስምምነት ደግሞ በቃል ወይም በጽሁፍ ሊሆን ይችላል።

**ስራ ቦታ ያሎት መብት፡**

- የተቀጠሩበት ውል ስራ ከጀመሩበት ዕለት ጀምሮ ብ 2 ወር ውስጥ ብጽሁፍ ሊሰጦት ይገባል።
- ሁልግዜ በሚከፈሎት ግዜ; ፔይስሊፕ (የደሞዝ ክፍያ ማረጋገጫ) እንዲሰጦት መብት ኣሎት።
- በሕግ ኣንድ ሰው በሰኣት ሊከፈለው የተወሰነው ክፍያ ሊከፈሎት መብት ኣሎት
- ከደሞዝዎ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ገንዘብ እዳይቆረጥቦት መብት ኣሎት።
- ለሚወስዱት የእረፍት ክፍያ; ኣንድ ተቀጣሪ የሙሉ ሰኣት ተቀጣሪ ከሆነ በኣመት የ 28 ቀናት ማለት ነው። የግማሽ ግዜ ተቀጣሪዎች እንደ የሰኣቶቻቸው መጠን ይገባቸዋል።
- ሴቶች ለሚወስዱት የወሊድ እረፍት ክፍያ ይገባቸዋል የትዳር ኣጋራቸው ደግሞ ለሚወስዱት የኣባት እረፍት ክፍያ ይገባቸዋል።
- ምንም ኣይነት ማዳላት እንዳይደርስቦት መብት ኣሎት።
- ለሁለት ኣመት ተቀጥረው ሲሰሩ ከቆዩ እናም ደግሞ ከስራ ከተባረሩ ከኣሰሪዎ የተባረሩበትን ምክንያት በጽሁፍ እንዲሰጥዎት መብት ኣሎት። እርጉዝ የሆኑ ሴቶች ግን ወይም የወሊድ እረፍት ላይ ያሉ ሴቶች ምንም ያህል ግዜ ቢሰሩም ማስረጃ ምክንያት ብጽሁፍ እንዲሰጣቸው መብት ኣላቸው።
- ለሁለት ኣመት ተቀጥረው ሲሰሩ ከቆዩ እናም ደግሞ ከስራ ያለ በቂ ምክንያት ከተባረሩ የካሳ ክፍያ እንዲከፈሎት መብት ኣሎት።
- የግማሽ ግዜ ተቀጣሪዎች እንደ ሙሉ ሰኣት ተቀጣሪዎች ኣንድ ኣይነት መብት ኣላቸው።

እነዚህን በተመለከተ እርስዎን የሚመለከትዎት የትኛው እነደሆነ እርግጠኛ ካልሆኑ የሚከተሉትን በማግኘት ያጣሩ፡


- ለዜጎች ማስረጃን የሚሰጥ ድርጅት በድረገጽ **www.cas.org.uk** ወይም ደግሞ በኣካባቢዎ የሚገኘው ቢሮዋቸው ይደውሉላቸው።
- ምክር የሚሰጥ; የዕርቅ እና ዳኝነት ኣገልግሎት (ኤሲኤኤስ) ተብሎም የሚጠራውን ድረጅት በድረገጽ **www.acas.org.uk** ወይም ደግሞ በስልክ ቁጥር 0300 123 1100 ይደውሉላቸው።



# የወንጀል ሰለባ ለሆኑ

–

# ስኮትላንድ ውስጥ ወንጀል የሚባሉት



# የወንጀል ሰለባ ለሆኑ

የሆነ ሰው ወንጀለኛ ሊሆን ይችላል እድሜው ሆነ ጾታው ወይ ብሄሩ ምን መሆኑ ኣጠያያቂ ሳይሆን። ኣንድ ሰው የወንጀል ሰለባ ሊሆን የሚችለው በኣካላዊ ወይም ስሜታዊ በሆነ መንገድ ወይም ደግሞ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ጥቃት ሲያጋጥመው ነው።

የወንጀል ሰለባ ከሆኑ ለሆነ ሰው ለመንገር ኣይፍሩ; በኣስቸኳይ ስላጋጠሞት ሁኔታ ለሆነ ሰው ከነገሩ ችግሩ ሊያቆም ይችላል እርዳታም ሊያገኙ የሚችሉበት መንገድ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ ማለት ደግሞ ለቤተሰብ ሊነግሩ ይችላሉ ወይም ደግሞ ለጓደኞችዎ ወይም ለፖሊስ ሊነግሩ ይችላሉ።

የወንጀል ሰለባ ከሆኑ ኣንዳንድ መብት ኣሎት እርሱም የሚያጠቃልለው ስለ ጉዳይዎ በተመለከተ ሁሉን ማወቅ እና እርዳታም ለማግኘት። ጉዳይዎን በተመለከተ የሚከታተሉልዎት ሁሉም ወገኖች; ጉዳይዎ ወደ ፍርድ ቤት ከተመራ በኣግባቡ እና በክብር ሊያስተናግዱዎት ይገባል።

ስኮትላንድ ውስጥ የወንጀል ሰለባ ከሆኑ ወይም የሚያውቁጥ የወንጀል ሰለባ የሆነ ሌላ ሰው ካለ; ማስረጃ ምክርና እርዳታ ሊሰጡ የሚችሉ ብዙ ድርጅቶች ኣሉ እነዚህንም ድርጅቶች የነጻ በሆነ ስልክ ላይ ሊደውሉላቸው ይችላሉ። ኣብዛኞቹም ሚስጥራዊ በሆነ ኣሰራር ነው የሚሰሩት በራስዎ መተማመን መልሰው እንዲችሉ እርዳታ ሊሰጡዎት ይችላሉ የእለት ከእለት ኑሮዎንም በተመለከተ እርዳታ ሊሰጡዎት ይችላሉ። ከእነዚህ ድርጅቶችም ውስጥ የኣንዳንዶቹን ማስረጃ ከዚህ የማስረጃ ወረቀት በጀርባው በኩል ሊያገኙት ይችላሉ።



# ስኮትላንድ ውስጥ ወንጀል የሚባሉት

## ጥቃት

ጥቃት ማለት በሌላ ሰው ላይ ጥቃት ሲደርስበት ነው። ኣብዛኛውን ግዜ ኣካላዊ ጥቃት ሲደርስበት ነው። ይህ ማለት ደግሞ ጥቃቱ በሕግ ጥቃት ተብሎ እንዲታይ የግድ ጉዳቱ የተፈጸመ መሆን የለበትም። የተፈጸመው ጥቃት በእጅ ወይም በእግር የተደረገ ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ በሆነ እቃ እንደ እንጨት ድንጋይ ወይም ቢላ ሊሆን ይችላል። የሆነ ሰው ከተፋብዎት ወይም ውሻውን እንደሚልክብዎት ከዛተ እንደ ጥቃት ይቆጠራል።

ከበድ ያለ ጥቃት ከሆኑ እንደ ትልቅ ወንጀል ነው የሚታየው። የተፈጸመው ጥቃት በተለያየ መልኩ ከበድ ያለ ጥቃት ሊባል ይችላል ለምሳሌ የተፈጸመው ጥቃት በሆነ መሳርያ ከነበረ; የጥቃቱ ሰለባ የነበሩት ኣረጋውያን ወይም ልጆች ከነበሩ; ወይም ደግሞ ጥቃቱ ያጋጠማቸው እቤታቸው እያሉ ከነበረ።

## ጠመንጃ እና ሽጉጥ

ስኮትላንድ ውስጥ የ "ጠመንጃ እና ሽጉጥ ባህል" የለም። ስኮትላንድ ውስጥ የጠመንጃ እና ሽጉጥ ፍቃድ ካለዎት ብቻ ነው ጠመንጃ እና ሽጉጥ እንዲይዙ የሚፈቀድሎት። የጠመንጃ እና ሽጉጥ ያለ ፍቃድ ይዘው ከተገኙ እንደ ትልቅ ወንጀል ስለሚወሰድ በሱ ምክንያት የእስር ፍርድ ሊፈረድቦት ይችላል።

## የሚጎዱ መሳርያዎች

ሊጎዳ የሚችል መሳርያ; ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መሳርያ እንደ ቢላ እና ጠመንጃ እና ሽጉጥ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

ሊጎዳ የሚችል መሳርያ በተለይ ቢላ ሰው የሚበዛበት ኣካባቢ በፍጹም ሊይዙ ኣይፈቀድም። ቢላ ይዞ የተገኘ ሰው ሊፈረድበት የሚችለው ትልቁ መቀጮ 5 ዓመት የእስር ፍርድ ነው።

የሆነ ጥቃት ከፈጸሙ በቢላ በተደረገ ጥቃትም ደግሞ ሰው ከሞተ የዕድሜ ልክ እስር ሊፈረድቦት ይችላል። የደረሰውን ጥቃት የፈጸሙት እርስዎ ባይሆኑም ግን ጥቃት የፈጸመው ሰው ቢላ እንደያዘ ኣውቀው ከነበር ቢላውንም ሊጠቀምበት እንደሚችል ኣውቀው ከነበር ፍርዱ የዕድሜ ልክ እስር ነው የሚሆነው።

## ግብረስጋ ነክ ወንጀል

ኣንድ ሰው ያለ ፍቃድ በሌላኛው ሰው ላይ የግብረስጋ ግኑኝነት ከፈጸመ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ነው የፈጸመው ማለት ነው። የሆነ ሰው የኣስገድዶ መድፈር ተጠቂ ሊሆን ይችላል። ጾታው እድሜው ወይም የቆዳው ኣይነት ምንም ይሁን በማያጠያይቅ ሁኔታ። የአስገድዶ መድፈር ወንጀል በማይተዋወቁ ሰሰዎች; በጓደኞች መካከል ወይም ደግሞ በቤተሰብ መካከል ወይም በእጮኛሞች እና በትዳር ጓደኞሞች መካከል ሊያጋጥም ይችላል።

ስኮትላንድ ውስጥ ኣንድ ሰው የግብረስጋ ግኑኝነት ለማድረግ በሕግ 16 ኣመት የሞላው መሆን ኣለበት።

ኣንድ ሰው ያለ ፍቃድ በሌላኛው ሰው ላይ የግብረስጋ ግኑኝነት ከፈጸመ ወንጀል ነው የፈጸመው ማለት ነው።

ኣንድን ሰው ወንድ ሆነ ሴት ኣስገድዶ መድፈር ወንጀል ነው።

አስገድዶ መድፈር ሰለባ ከሆኑ ከሚከተሉት እታች የተዘረዘሩት ድርጅቶች እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ:

- **የአስገድዶ መድፈር ችግር ስስኮትላንድ** – 08088 010 302
- **ሰለባ ለሆኑ እርዳታ ስኮትላንድ** – 0345 603 9213
- **ፖሊስ ስኮትላንድ** - 101 (ኣስቸኳይ ካልሆነ) 999 (ኣስቸኳይ ከሆነ)

## ሽርሙጥና

ሽርሙጥና ማለት የግብረስጋ ግኑኝነትን እንደስራ ኣድርጎ ገንዘብ ወይም ደግሞ ሌላ ጥቅም ለማግኘት መሞከር ማለት ነው። ሽርሙጥና ላይ ተሳትፎ የሚሰራውም ሆነ ከፍሎ የግብረስጋ ግኑኝነት ለማድረግ የፈለገው ሰው መቀጮ ፍርድ ሊሰጠው ይችላል።

## በጥላቻ የሚደረግ ወንጀል

"በጥላቻ የሚደረግ ወንጀል" ማለት ኣንድ ሰው ላይ ወይም ንብረት ላይ በጥላቻ ወይም ንዴት ምክንያት እዛ ሰው ላይ ወይም ኣንድ የሆነ ቡድን ላይ ጥቃት ሲደርስባቸው ነው።

**እነዚህ እታች በተዘረዘሩት ምክንያት ኣንድ ሰው ጥቃት ካደረሰቦት; በጥላቻ የሚደረግ ወንጀል ሰለባ ኖት ማለት ነው:**

- ብሄር
- ሃይማኖት
- የግብረስጋ ግኑኝነት ዝንባሌዎት
- ጾታዎን የቀየሩ ሰው ከሆኑ
- ኣካለ ስንኩል ከሆኑ

**በጥላቻ የሚደረግ ወንጀል በተወሰነ ብቻ ሳይሆን በተለያየ መልኩ ሊፈጸም ይችላል:**

- ግድያ
- ኣካላዊ ጥቃት
- ንብረት ማበላሸት ለምሳሌ ስእል ወይም ጽሁፍ እግድግዳ ላይ መማድረግ; በእሳት ማቃጠል እና ማውደም
- የሚያስፈራራ ወይም ደግሞ የሚያሳስብ ባህሪ ቅጥ የሌለው ኣይነት ተግባራት ወይም ስልክ በመደወል የሚደረግ ኣጸያፊ ተግባራት
- ቅር የሚያሰኝ ደብዳቤ; ጽሁፍ ወረቀት; ፖስተር (የሚለጠፍ ማስታወቂያ)
- በቃል የሚደረግ ጥቃት ወይም ደግሞ ማዋረድ እና ስድብ
- በኢንተርኔት የሚደረግ ጥቃት እና ስድብ

**ኣስቸኳይ ያልሆኑ ኣጋጣሚዎችን ለፖሊስ በሚከተሉት ደውለው ሊያሳውቁ ይችላሉ:**

- **999** ኣስቸኳይ ከሆነ ወይ ደግሞ **101** ኣስቸኳይ ካልሆነ
- ወይም ደግሞ በኢንተርኔት ላይ በጥላቻ ለሚደረግ ወንጀል ቅሬታ ማቅረቢያ ፎርም ከስኮትላንድ ፖሊስ ድረ ገጽ ወይም ከሚከተለው ድረ ገጽ ማስረጃ በመውሰድ ሊያሳውቁ ይችላሉ **http://www.scotland.police.uk/contact-us/hate-crime-and-third-party-reporting/**

## ለጥቅም ብሎ ሰውን በኮንትሮባንድ ማሸጋገር

ለጥቅም ብሎ ሰውን በኮንትሮባንድ ማሸጋገር ወንጀል ነው ኣብዛኛውን ግዜም ከሌላ ወንጀል እንደ ሽርሙጥና; እንደ ሃሺሽ የመሳሰሉ ኣደንዛዥ ዕጽ; ሕገወጥ የገንዘብ ማሸጋገር ጋር የተያያዘ ነው። ለጥቅም ብሎ ሰውን በኮንትሮባንድ የማሸጋገር ሰለባ የሆኑ ሰዎች በተለያየ ምክንያት በቀላሉ ለችግር የተጋጡ ሊሆኑ ይችላሉ ለምሳሌ በመኖሪያ ፍቃድ እና የገንዘብ ችግር; በኣመጧቸው ሰዎች ማስፈራራት ጥቃት እና በደል ሊያጋጥማቸው ይችላል።

ለጥቅም ብሎ ሰውን በኮንትሮባንድ የማሸጋገር ሰለባ ከሆኑ ለፖሊስ ወይም ደግሞ ለጥቅም ብሎ ሰውን በኮንትሮባንድ የማሸጋገር ጉዳቱን የሚያሳውቁ ድርጅት (ታራ) በስልክ ቁጥር 0141 276 7724 ይደውሉላቸው።

## እንደ ሃሺሽ የመሳሰሉ ኣደንዛዥ ዕጽ

እንደ ሃሺሽ የመሳሰሉ ኣደንዛዥ ዕጽ መውሰድ እስከ ሞት የሚያደርስ ከባድ የጤና ችግር ሊያስከትል ይችላል።

በሕግ ቁጥጥር የሚደረግላቸው ሁለት ኣይነት ኣደንዛዥ እጾች ኣሉ፡ ኣንደኛው ኣይነት ፈጽሞ ሕገወጥ የሆኑት ናቸው (ለምሳሌ ካናቢስ; ሂሮይን; ኤስተሲ; ኮኬን; ጫት ወዘተ) ሌላኛው ኣይነት ደግሞ ያለ ሓኪም ትእዛዝ ወይም የጥርስ ሓኪም ከወሰዱ ሕገወጥ የሆኑ ናቸው (ለምሳሌ ሞርፊን; ሜታሞርፊን ወዘተ)

በሕግ ቁጥጥር የሚደረግላቸው ኣደንዛዥ እጽ ይዘው ከተገኙ ወይም ለሌሎች በሕግ ቁጥጥር የሚደረግላቸው ኣደንዛዥ እጽ ከሰጡ ሕገወጥ ነው። በሕግ ቁጥጥር የሚደረግላቸው ኣደንዛዥ እጽ ሲሸጡ ከተገኙ ሕገወጥ ነው።

የካናቢስ ተክል የሚያሳድጉ ከሆነ ወይም የሌላ ሰው የካናቢስ ተክል ለማሳደግ የሚያግዙ ከሆነ ሕገወጥ ነው።

ምንም ኣይነት በሕግ ቁጥጥር የሚደረግላቸው የኣደንዛዥ እጽ ስራ ላይ ከተሳተፉ ሕገወጥ ነው።

“በሕግ የማይፈቀዱ ኣደንዛዥ እጽ” ተብለው የሚጠሩ ሳይኮኣክቲቭ ሰብስታንስ (የኣንጎልን ኣሰራር የሚቀይሩ) ኣደገኛ ናቸው ፈጽመው ሊወስዱ ኣይገባም። ለሌላ ሰው ከሸጡ ወይም ከሰጡ ሕግ ጥሰዋል ማለት ነው።



## በሕገወጥ መንገድ ገንዘብ ማሸጋገር

በወንጀል የተገኘን ገንዘብ መውሰድ ወይም መጠቀም ወንጀል ነው።



## ስርቆት



ስርቆት የሌላን ሰው ንብረት ያለ ኣግባብ እና ያለ ፍቃድ በመውሰድ የሚደረግ ወንጀል ነው። የስርቆት ምሳሌ እንደሚከተለው፡

- ከሱቅ ውስጥ መስረቅ
- ቤት ውስጥ ገብቶ መስረቅ
- ከሌላ ሰው ኣትክልት ወይም ግቢ እቃ መውሰድ
- መኪና መስረቅ

እንደተሰረቀ እያወቁ ወይም እየጠረጠሩ ኣንድ እቃን ይዘው ከተገኙ ይህም ወንጀል ነው የሚታየው; የሌባ ተቀባይ ተብሎም ይታወቃል። ስኮትላንድ ውስጥ ስርቆት በሕግ ወንጀል ነው።

## የኢንተርኔት መገናኛ እንደ ፌስቡክ

በኢንተርኔት መገናኛ የሚያስፈራራ; የማጥቃት ወይም ቅጥ የሌለው ኣይነት መልእክት ወይም ደግሞ ፎቶ እና ስእል በፌስቡክ; ትዊተር ወይም በሆነ በሌላ የኢንተርኔት መገናኛ መንገድ በመላክ የሚደረግ ወንጀል ነው። ይህም ደግሞ በመገናኛ መንገድ የሚደረግ ጉዳት; ጥቃት የሚያዋርድ ስድብ ወይም ኣንዳንዴ በጥላቻ የሚደረግ ወንጀል ተብሎ ይጠራል።

እንደነዚህ የመሳሰሉ የሆኑ ሁኔታዎችን ለፖሊስ ቅራኔ በኢንተርኔት መገናኛ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ወንጀል ፈጻሚውን ከኢንተርኔት መገናኛው ሊያስወጡት ይችላሉ ወይም እሱ የሚጠቀምበትን የኢንተርኔት መገናኛ ኣድራሻ ሊዘጉት ይችላሉ።

## ብእንስሳዎች ላይ በደል ማድረስ

ብእንስሳዎች ላይ በደል ማድረስ ወንጀል ነው።

**እንስሳ ካሎት የሚከተሉትን ማድረግ ኣለቦት፡**

- ንጹህ እና ምቾት ያለው ቦታ ማዘጋጀት ኣለቦት
- ንጹህ እና ምቾት ያለው መተኛ ቦታ ማዘጋጀት ኣለቦት
- ብቁ ውሃና ምግብን ማዘጋጀት ኣለቦት
- እንስሳው ከታመመ ወይም ከተጎዳ ሕክምና ማዘጋጀት ኣለቦት

## የወንጀል ሰለባ ለሆኑ እርዳታ

**ፖሊስ ስኮትላንድ**
የስልክ ቁጥር፡ 999 ድረ ገጽ፡
የስልክ ቁጥር፡ 101 (አስቸኳይ ያልሆነ)
ድረ ገጽ፡ **www.scotland.police.uk**

**ስኮቲሽ ሬፊዩጂ ካውንስል**
የስልክ ቁጥር፡ 0141 248 9799
ድረ ገጽ፡ **www.scottishrefugeecouncil.org.uk**

**ቪክትም ሰፖርት ስኮትላንድ**
የስልክ ቁጥር፡ 0345 603 9213 ወይም 0808 16 89 111
ከ ሰኞ 8 ሰኣት ከጠዋቱ እስከ ማታ 8 ሰኣት
ድረ ገጽ፡ **www.victimsupportsco.org.uk**

**ሬፕ ክራይሰስ ስኮትላንድ**
የስልክ ቁጥር፡ 08088 01 03 02
ድረ ገጽ፡ **www.rapecrisisscotland.org.uk**
በሂወታቸው በሆነ ወቅት የመደፈር ችግር ኣጋጥሙዋቸው ለነበሩ ለሆኑ ሰዎች የነጻ እና ሚስጥራዊ እርዳታ ይሰጣሉ። ወደ ዋናው ሃገራዊ ቢሮዋቸው በስልክ ቁጥር 0141 331 4180 ከደወሉ ወደ ኣካባቢዎ ያለው ሬፕ ክራይስስ ሴንተር ወደሚባለው እርዳታ እንዲያገኙ ሊመሩዋቹ ይችላሉ።

**ስኮቲሽ ዉሜንስ ኤድ**
የስልክ ቁጥር፡ 0131 226 6606
ድረ ገጽ፡ **www.scottishwomensaid.org.uk**
የቤት ውስጥ በደል ኣጋጥሙዋቸው ለነበሩ ለሆኑ ሴቶች ወይም በእንደሱ ኣይነት ሁኔታ ላይ ላሉ ምክር; እርዳታ ደህንነት ያለው የመኖሪያ ቤት ይሰጣሉ። ሁሉም ድርጅቶች ደግሞ ለልጆች እና ጎልማሳዎች እርዳታ የሚሰጡ ሰራተኞች ኣሉዋቸው።

**ቻይልድላይን ስኮትላንድ**
የስልክ ቁጥር፡ 0800 1111 (7 ቀን በሳምንት 24 ሰኣታት ክፍት ናቸው)
ድረ ገጽ፡ **www.childline.org.uk**
ለልጆች እርዳታ እና ምክር ይሰጣሉ።

**ሲትዝን ኣድቫይስ ቢሮ**
ድረ ገጽ፡ **www.cas.org.uk**
ስለ መብትዎ ምክር ይሰጣሉ። ይህ ድረ ገጽ በኣካባቢዎ ያሉትን ሲትዝንስ ኣድቫይስ ቢሮ እንዴት ኣድርገው ሊያገኙዋቸው እንደሚችሉ ሊነግሮት ይችላል።

**ዘ ሳማሪታንስ**
የስልክ ቁጥር፡ 08457 909090
ድረ ገጽ፡ **www.samaritans.org**
ችግር ላለበት ለሆነ ሰው እርዳታ ይሰጣሉ።

**ስኮቲሽ ዶመስቲክ ኣብዩዝ**
የስልክ ቁጥር፡ 0800 027 1234 (24 ሰኣታት ክፍት የሆነ መስመር ነው)
ድረ ገጽ፡ **www.sdah.org.uk**
የቤት ውስጥ በደል ኣጋጥሙዋቸው ለነበሩ ለሆኑ ሰዎች ሚስጥራዊ ምክር እና እርዳታ ይሰጣሉ። ይህ ለመደወል ነጻ የሆነ የስልክ ቁጥር የሂሳብ መክፈያ ደረሰኝ ላይ ኣይወጣም።

**ሼልተር**
የስልክ ቁጥር፡ 0808 800 4444
ድረ ገጽ፡ **scotland.shelter.org.uk**
ቤት መፈለግን በተመለከተ ኣጠቃላይ ማስረጃ እና ለግዜው የኣስቸኳይ ደህንነት ያለው ቤት እንዴት ሊያገኙ እንደሚችሉ ማስረጃ ይሰጣሉ።




## ስለ ስኮትላንድ ሕጎችን ለማወቅ ተጨማሪ ማስረጃ ለማግኘት ወደ ሚከተለው ይመልከቱ፡

**www.nclanarkshire.ac.uk/scotslaw**

## ከሌሎች ጋር ተወያዩ

ኒው ኮሌጅ ላናርሻየርን ፌስቡክ ላይ ኣግኙዋቸው፡

**facebook.com/NCLanarkshire**

**@NCLanarkshire**

### ሕጋዊ መመርያ

እዚ የማስረጃ ወረቀት ላይ ያለው ማስረጃ ሙሉ ዝርዝር የሕጉ መመርያ ሳይሆን ነገር ግን እንደ ኣጠቃላይ መመርያ እንዲጠቅሙዎት በማለት ነው። ስኮትላንድ የራስዋ የምትመራበት ሕጋዊ መመርያ ኣላት ስለዚህም ስኮትላንድ ውስጥ ያለው  ሕግ ምናልባት ከሌላ እንግሊዝ ኣገር ያሉ ክፍሎች የተለየ ሊሆን ይችላል።የሆነ ሕጋዊ ኣገልግሎት የሚያስፈልጎት ከሆነ ከጠበቃዎ ወይም ስኮትላንድ ካለው ሲትዝንስ ኣድቫይዝ ቢሮ (ለዜጎች ማስረጃ የሚሰጥ ድርጅት) ጋር ተገናኙ።

**እባክዎን ያስተውሉ፡** እዚህ ሕትመት ላይ ያለው ሁሉም ማስረጃ በታተመበት ወቅት የነበረ ትክክለኛ ማስረጃ ነው። ንኒው ኮሌጅ ላናርሻየር፡ የበጎ ኣድራጎት ድርጅት የምዝገባ ቁጥር: SC021206

New College Lanarkshire